# "በእኔ ስም አይሆነም!"
# "NON IN MIO NOME"

በልጅግ ዓሊ

## ክፍል አንድ
## ሕዝብን የጨፈጨፈ ገዳይ ጀግና አይደለም!

ልቤ ተሸበረ ከሩቅ ስትጣሪ ሰማሁሽ ሃገሬ፣
ስንቱን ብሶት ላውራሽ እናቴ ዘርዝሬ፣ . . . .

ሀገሬ ድምጽሽን ቀርቤ እንዳልሰማ ፤
አላጥፍ አልጠቀልል መሬት አይደለም ሻማ
ክል እያለ መጥቶ የዝማሬሽ ቃና
ያማልለኝ ገባ ያዘናጋኝ ገባ ከሩቄ ሆነና።

ከሩቅ ቢሆንም ድምጽሽ እንኳን አልጠፋ
ሕያው ያደረገኝ ነፍሴን ያወጀልኝ ነው የልቤ ተስፋ።

ዮሐንስ አድማሱ
ልቤ ተሸበረ /1957




ጣሊያን ቲቮሊ ከተማ የሚገኘው ፍርድ ቤት ሜይ 6/2014 በሰዎች ተሞልቷል። ፍርድ ቤቱ ፍርዱን በሚከታተሉ በመሙላቱ ምክንያት ከፍርድቤቱ ውጭ የፋሽሽቶች ደጋፊዎችም ይሁኑ ተቃዋሚዎች ተሰባስበዋል።

ዳኛው በሦስቱ ወጣቶች በእነ
**1ኛ. ጆቫኒ ትራሰቱሊ - Giovanni Trastulli(1985),**
**2ኛ. ፔርፓውሎ ዚቪ - Pierpaolo Zivi(1993),**
**3ኛ.ሲሞንሉካ ፕሮካችአንቲ - Simonluca Procaccianti(1988)**

ላይ በአፊሌ ከተማ ከንቲባ **ኤርኮሊ ቪሪ( Ercole Viri)** በተመሠረተው ክስ የመጨረሻውን ፍርድ ለመስጠት ተዘጋጅተዋል። ክሱ በቅርብ በተሰራው የማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒ ሐውልት ላይ "ሕዝብ የጨፈጨፈ ጀግና ሊሆን አይችልም" የሚል መፈክር ወጣቶቹ በትልቁ በመጻፋቸው ምክንያት ነበር።




ከሳሾች በአፊሌ ከተማ ከንቲባ መሪነት ፋሽሽቶችን የሚደግፉ ናቸው። ይህ ድጋፋቸው የኛ ነዋሪ ነበር የሚሉትን ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒን ሃውልት እስከ መስራት አድርሷቸዋል። ለድጋፋቸው ምክንያት የሆነው ማርሻል ግራዚያኒ "ሃገሩን ያገለገለ ወታደር ሲሆን ትዕዛዝ ከበላይ የሚቀበል ብቻ የነበረና ሃገሩን የሚወድ ነው" የሚል ነው። "ስለሆነ ለኢጣሊያን ጀግና ነው።" "የእሱን ሃውልት ማበላሸት የኢጣሊያንን ቅርስ እንደማበላሸት ይቆጠራል" የሚል ክስ ነበር ያቀረቡት (ከሞላ ጎደል)።

የወጣቶቹ ጠበቃ ሮዶልፍ ግራዚያኒ የፈፀማቸዉን ግፍና ጭፍጨፋ አስመልክተው ተጨባጭ መረጃዎችን አንድ በአንድ እየገለፁ ለዳኛዉ አቅርበው ዳኛውም ብዙ ትንተና ከሰጡ በኋላ የኢጣሊያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ አሥራ አንድን ጠቅሰው፣ የአሁኑ የጣሊያን መንግሥት ከዚህ በፊት የተደረጉትን ወረራዎች በመቃወም የተመሰረተ በመሆኑና ግራዚያኒም ጀግና ሆኖ ሊቆጠር የሚገባው ባለመሆኑ ሦስቱን ወጣቶች  በነጻ ለቅቄአለሁ ብለው ፍርድ ሰጥተዋል። ከፍርድቤት ውስጥም ይሁን ከፍርድ ቤቱ ውጭ የተሰበሰበው የፋሽሽቶች ተቃዋሚ ደስታውን ሲገልጽ፣ ፋሽሽቶች ደግሞ አንገታቸውን ደፍተው ተመልሰዋል።

ትግሉ አልቆመም ቀጥሏል!!!

በዚህ ፍርድ የዚህ ሃውልት ጉዳይ አሁንም አላለቀም። በፋሽሽቶች ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል ሃውልቱ




መፍረስ አለበት፣ የለበትም በሚል ትግሉ ቀጥሏል። አፍሌ ከተማ ከሮም 50 ኪሎሜትር ወደ ምሥራቅ ሲጓዙ በተራራ ጫፍ ላይ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነች። በዚህ ከተማ ውስጥ ነው ፋሽሽቱ ግራዚያኒ የሕይወቱን የመጨረሻ ዘመናት የኖረው። በዚህም ምክንያት ነው የፋሽሽት ደጋፊዎች ከተማዋ ጫፍ አካባቢ በሚገኝ አንድ ኮረብታ ላይ የግራዚያኒ ማስታወሻ የሠሩት።

እዚህ ቦታ ላይ ቆሜ በፋሽሽቶች በመርዝ ጢስ ሳይቀር የተጨፈጨፉትን ዜጎቻችንን ሳስበው እነ ሞገስ አስገዶም፣ እነ አብርሃም ደቦጭ በግራዚያኒ ላይ እንዳደረጉት በፈንጂ ይህንን ግንብ አፍርሰው፣ አፍርሰው ነው ያለኝ። ይህ የስንት ሴቶችን፣ አቅመ ደካሞችን፣ ሕጻናትን ደም ያፈሰሰ ፋሽሽት ሊወገዝ ሲገባው ምክንያት እየተፈለገ መታሰቢያ ሃውልት ሊቆምለት አይገባም ነበር። ዛሬ እንደ ትላንቱ ለእነዚህ በግፍ ለተጨፈጨፉት ዜጎቻችን የሚቆም ሃያል መንግሥት ጠፍቶ፣ ይህ ሐውልት መቆሙ በሰማዕታቱም ላይ አሁንም ግፍ እየተሠራባቸው እንደሆነ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ለሒትለር በአሁኑ ወቅት በጀርመን ሃገር አንድ ሃውልት ቢሰራለት እስራዔላውያን ከዳር እስከ ዳር ይነሱ ነበር። ሃያላን መንግሥታትም ስንት መግለጫ በሰጡ ነበር።

በኢጣሊያን ወረራ አልተሳተፈችም በሚል የሚነገርላትም ቫቲካን በሚያስገርም ሁኔታ ዝምታን መርጣለች። ይባስ ተብሎ አሁንም እንደ ጦርነቱ ጊዜ በሃውልቱ ምረቃ ላይ የቫቲካን ቄስ ተገኝተዋል። ቫቲካን ዛሬም ይህንን ሐውልት በሚመለከት በተደጋጋሚ ከሃገር ወዳዶች ቢጻፍላትም እንደ ጦርነቱ ወቅት ከፋሽሽቶቹ ማበርን መርጣለች።




ትግሉ ግን አሁንም አልቆመም። ቀጥሏል!!!

አፊሌ ከተማ ውስጥ የዚህን ሐውልት መፍረስ በሚመለከት በዴሞክራቲክ ፓርቲው ጽሕፈት ቤት ውስጥ የተደረገው ስብሰባ ላይ ተግኝቻለሁ። 20 የሚሆኑ ሰዎች በዚህ ትንሽ ጠባብ ክፍል ውስጥ የጦፈ ክርክር ሲደርጉም ነበር። ሰኔ 28/2014 አፊሌ ውስጥ ስለሚደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ነበር ውይይቱ። ከብዙ ውይይት በኋላ አመቺ ነው ብለው ባመኑበት ተስማምተው ስብሰባው አለቀ። ከስብሰባው ወጥተን ወደ ሮማ በምንመለስበት ጊዜ የአፊሌ ከተማ ከንቲባ ያሰማራቸው የፋሽሽት ደጋፊዎች የሞሶሎኒ ፍቶ የተሰቀለበት ቡና ቤት ውስጥ ተሰብስበው ያሽካኩ እንደነበር ተመልክቻለሁ።



የአፊሌ ከተማ ከንቲባ ይህንን ሃውልት በመሥራት ቱሪስቶችን በመሳብ ከተማችንን እናሳድጋለን በማለት ለከተማው ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ ቅስቀሳ እያደረገ ነው። በዚህም የአፊሌ ከተማ ነዋሪዎችን ድጋፍ ማሰባሰቡን ቀጥሏል። ይህ ከንቲባ **"ኢትዮጵያኖች ከመቼ ጀምሮ ነው ስለ ታሪካቸው የሚያስቡት"** በማለት ተሳልቋል። አዎ እውነቱን ነው። ጣሊያን የተዋጉትን ጀግኖቻችንን የኛው ፋሽሽቶች ረሽነው በአንድ ጉድጓድ ቀብረዋቸዋል። አዎ የኛን ጀግኖች የመቃብር ቦታ ዳዋ በልቶታል። አዎ ጀግኖቻችን እኛው ራሳችን አዋርደናቸዋል። ዛሬ ስለ አደዋ መዝፈን ወንጀል ነው ። ዛሬ ስለ ምኒሊክ መናገር ዘረኝነት ነው፣ ተብሏል። አዎ ታሪካችን ተዛብቶ አሁን እየተጻፈ ነው። አዎ ዛሬ ከሆዳቸው አርቀው ማሰብ የማይችሉ ዘረኞች ሥልጣኑን ይዘውታል።

ቢሆንም እነዚያ በግፍ የተጨፈጨፉ ዜጎቻችን ወዳጅ አላጡም። የጣሊያን ዴሞክራቶች፣ የጣሊያን ኮምኒስቶች፣ የጣሊያን ራስ ተፈሪያን፣ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ፣ ዓለም አቀፍ ትብብር ለፍትህ፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና ሌሎችም በቆራጥነት ተታግለው ለሐውልቱ ማሰሪያ የተመደበውን 127 ሺህ ኤሮ አሳግደዋል።

ትግሉ ግን አሁንም ቀጥሏል!!

እዛች ትንሽ የዴሞክራቲክ ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ሆኜ እየተንገበገቡ ፋሽዝምን የሚያወግዙ ጀግና ወጣት ጣሊያኖችን ሳስብ የኛ ወጣቶችን ኑሮ በጣሊያን አንድ ጊዜ ማሰቤ አልቀረም። ጣሊያን ውስጥ ያየሁትን የወጣት ዜጎቻችንን የሞራል ድቀት የትም ሃገር አላየሁትም። ሳህራ በረሃ ውስጥ የጀግንነት ስሜት ይሰማቸው የነበሩትን ወጣቶች ችግሩን አልፈው፣ ባሕሩን አቋርጠው፣ ያ የጠበቁት የአውሮፓ ኑሮ ሳያገኙት ሲቀሩ እንኳን

ለሃገራቸው ለራሳቸውም ማሰብ ባይችሉ የሚገርም አይሆንም። በጣሊያን የወጣቶቻችንን ኑሮ በሌላ ክፍል እመለስበታለሁ።

በዚህች ትንሽ ክፍል ውስጥ ትልቁ የመታገያ መፈክራቸው በሰፊው ተጽፏል። "NON IN MIO NOME"። "በእኔ ስም አይሆንም።" በጣሊያን ሕዝብ ስም፣ በጣሊያን ሕዝብ በተከፈለ ቀረጥ ግራዚያኒን የመሰሉ ፋሽሽቶች የሚታሰቡበት ሃውልት መሠራት የለበትም የሚሉ ታጋዮች እልከ አስጨራሽ ትግሉን ቀጥለውታል። በእኔ ስም አይሆንም ፣ በእኔ ስም አይደረግም በማለት ትግላቸውን አጧጡፈውታል። ፋሽሽቶች ታሪካቸውን የሚያስተባብሉበት መድረክ እንዳይሰጣቸው ሃያና ሰላሳ ዓመት ያልሆናቸው ወጣቶች በቆራጥነት ሲታገሉ ስናይ እኛስ ከፋሽስዝም ጋር ያለን ግንኙነት ምን ይመስላል? ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። የጨፍጫፊዎችን ማስተባቢያን ለገንዘብ ብለን ስናትም፣ ስንሸጥ፣ ስናሻስጥ የምንኖር ስንት ነን? በሕዝብ ደም እጁ የተጨማለቀውን ሁሉ ሃገር ወዳድ በሚል ስናቅፍ ስንሸከም የምንኖር ስንት ነን?

ግራዚያኒ ለሃገሩ ነው የተዋጋው የሚለውን የማይረባ ፕሮፖጋንዳ እነዚህ ወጣቶች አይቀበሉት። ስለዚህም ነው "ሕዝብን የጨፈጨፈ ጀግና አይደለም" ብለው የሚታገሉት። ግራዚያኒ ፋሽሽት ሰለሆነ በእኔ ስም ጀግና አይባልም ነው የሚሉት። ውቅያኖስ አቋርጠው ፣ በርሃውን ተሻግረው ፣ ዘመንንም ተሻግረው ፣ በአያት ፣ በቅድም አያቶቻቸው የተሰራውን ግፍ ነበር የሚቃወሙት። እኛስ በዘመናችን የተሠራው ግፍ ከደን ገዳዮችን ጀግና ስንል እንታያለን። ሁላችንም ራሳችንን እንጠይቅ። በሃገር ስም የሚሠሩ ግፎችን ምን ያህል እንደግፋለን? ለግራዚያኒ ካልሠራ ለሌላውም መሥራት የለበትም።

አሁንም በሌሎች ወጣቶች ደግሞ በተለየ መንገድ ትግሉ ቀጥሏል።

የኢጣሊያን ወጣትና ሕዝብ ሃቁን ለማስተማር ፣ አልፎም ተርፎ ለዓለም ሕዝብ ፍትሕ ሳያገኝ የቀረውን የጣሊያን የሃገራችንን ወረራ ለማጋለጥ በ2015 ለሕዝብ ሊቀርብ የታሰበ አንድ ዶክመንተሪ ፊልም ተጀምሯል። በዚህ ፊልም ላይ ብዙዎች ተሳትፈዋል። ይህ ፊልም "IF ONLY I WERE THAT WARRIOR" ይባላል። ስለ ፊልሙ ለመከታተል ለምትሹ እዚህ ታገኛላችሁ።

https://www.kickstarter.com/projects/awenfilms/if-only-i-were-that-warrior-a-documentary

ይህ ዶክመንተሪ ፊልም በሕዝብ እርዳት ነው የተሠራው አሁንም ቢሆን ወጣቶቹ እርዳታን ይሻሉ። እስቲ ሁላንም የምንችለውን በማድረግ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ እንሁን። ወደ ድረ ገጹ በመግባት ድጋፋችንን እንስጥ። ከንፈር ከመምጠጥ ያለፈ ድጋፋችን ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ይሆናልና እንተባበራቸው።

አሁንም ትግሉ ይቀጥላል!

# ገብረሥላሴ ደስታ
# ክፍል ሁለት

የኢጣሊያን ዋና ከተማ ሮምን ለመጎብኘት የግንቦት ወር ተመራጭነት ይኖረዋል። የበጋው ሃሩር ሳይጠነክር የክረምቱ ብርድ ለቀቅ እንዳደረገ ለስለስ ባለው ሙቀት ታይቶ የማያልቀውን የሮምን ታሪካዊ ቦታዎች በደንብ ማየት ይቻላል። ግንቦት ካለፈ ሰኔ ላይ ሐሩሩ ይጀምርና ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው መንቀሳቀስ ያደከማል።

በእንደዚህ ባለው የግንቦት አንዱን ቀን በእለተ እሁድ አንድ ሮማ ውስጥ የሚገኝ ኦንዳ ሮሳ የሚባል ኤፍ ኤም የሬዲዮ ጣቢያ እንድጎበኝ የተደረገልኝን ጥሪ ሳላቅማማ ነበር የተቀበልኩት። በዚህ ራዲዮ ጣቢያ ውስጥ አንዲት ዜጋችንና አንድ ጣሊያኒያዊ ዝግጅት ይዘው ቀርበዋል። የአማርኛ ዜና ሰምተን ከጨረስን በኋላ ጣሊያንያዊው ይጀምራል። በጣሊያንኛው ንግግር ውስጥ "ደብረ ሊባኖስ " እያለ እየደጋገመ ሲናገር እስማዋለሁ። ማህል ማህል "ሮዶልፎ ግራዚያኒ" የሚል ስምም ይሰማኛል። ከዛም "አፊሌ" የሚልም የማውቀው ቃል መጣ። የጋበዘኝን ግለሰብ ስለምንድነው ጣሊያኑ የሚወራው ብዬ ጠየቅሁት። በደፈናው ስለጣሊያን ወረራ ነው አለኝ ። "ደብረ ሊባኖስ" ሲል ሰማሁት ስለምንድነው ያወራው ብዬ አፋጥጬ ያዝኩ።

አሁን ይጨርሳል ያኔ ራሱኑ ትጠይቀዋለህ አለኝ። ሬዲዮኑን ጨርሶ ወደ እኛ ሲመጣ እንደ ዜጎቻቸችን ሰላምታ ደረት ለደረት አጋጨን. . . በዚች ትንሽ ቅስፈት የተተወቁት ጣሊያናዊ ሮማ ውስጥ በከረምኩበት ጊዜ ጥሩ ጓደኛ ሆኖ ሰነበተ። በጣሊያን ሃገር የሚደረገውን ጸረ ፋሽሽት እንቅስቃሴ ጠልቄ እንድረዳው አደረገኝ። እውቀታችን እየበዛ ሲመጣ ሃገራችንን በጣም የሚወድ ሰው ሆኖ አገኘሁት።



ይህ ሰው ካርሜሎ ክሬሼንቲ (Carmelo Crescenti). ይባላል። የጣሊያን ተወላጅ ነው። የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ተቀብሎ ተጠምቋል። የክርስትና ስሙ ገብረሥላሴ ነው። ለራሱ ደግሞ ደስታ የሚል ስም አውጥቶ በአሁኑ ወቅት ገብረሥላሴ ደስታ ተብሎ ይጠራል። ገብረሥላሴ በኢጣሊያን ሃገር ያሉ የራስተፈሪዎች ፌደሬሽን ሊቀመንበር ነው። ስለ ሃገራችን ታሪክ ከብዙዎቻችን የላቀ እውቀት አለው። ገብረሥላሴ የጀግኖችን ስም ሲጠራ ኩራት ይሰማዋል። አበበ አራጋይ፣ መስፍን ስለሺ፣ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም፣ ስምዖን አደፍርስ፣ አያና ብሩ፣ ዳባ ብሩ፣ በጅሮንድ ለጥይበሉ ገብሬ ፣ በሻህውረድ ሃብተወልድ፣ ሎሬንሶ ትእዛዝ ፣ መኮንን ድንቄ ፣ ተስፈዬ ተገኝ፣ ወዘተ . . . እነዚህ ስሞች ከነተግባራቸው ይኮራባቸዋል።

ገብረሥላሴ ደብረ ሊባኖስ ድረስ ሄዶ የአበበ አረጋይን መቃብር ተመልክቶ ክብሩን የገለጸ ነው። መግለጽ ብቻ ሳይሆን ዳዋ የለበሰውን የጀግናውን መቃብር አጽድቶ የመጣ ነው። ዛሬም ቢሆን የመቃብሩን ቦታ ለማደስ ያለው ራዕይ ትንሽም ቢሆን አልደከመም። ገብረሥላሴን በምታገኙበት ወቅት ሰላምታውን ሁሉ ተለውጦ እንደኛው ጉንጭ ለጉንጭ ሆኗል። በዚህ ቀን ገብረሥላሴ የደብረ ሊባኖስ ቀሳውስት የተፈጁበትን ወር ለማስታወስ ልዩ ዝግጅት አድርጎ ቀርቧል። ራሴን ጠየቅሁት፣ መቼ ነበር እልቂቱ ? ለምንስ ተፈጸመ? አፍረት ገባኝ። በዛ ቀን መከበሩን አይደለም፣ ጭፍጨፋው በዛ ወር መካሄዱን ረስቸዋለሁ። ለገብረ ሥላሴ ግን ለደቂቃ የሚረሳው አይደለም። ለመሆኑ ስንቶቻችን እናስታውሰዋለን። ብዙዎቻቸን ስለ አውሮፓ፣ ስለ ሰሜን አሜሪካ ሕዝብ ጦርነት ወዘተ እንጂ ስለ ሃገራችን እርግፍ አድርገን የተውን ይመስለኛል።

ለመሆኑ የደብረ ሊባኖስ ፍጅት ለምንድነው የተደረገው ? ብለን ስንጀምር የየካቲት 12 የአዲስ አበባው ፍጅት ይታወሰናል። ከፍጅቱ ጋር አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም ፣ ስምዖን አደፍርስ፣ ለጥይበሉ ገብሬ፣ አበበ አረጋይ፣ መስፍን ስለሺ፣ ታደሰ ጥሩነህ፣ በሻህውረድ ሃብተወልድ፣ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ወዘተ ይታወሱናል። ግራዚያኒ ላይ በተደረገው የመግደል ሙከራ አዲስ አበባ ውስጥ የተጨፈጨፉት ሰማዕታት ታሪክ የማይረሳ ነው።

ወሩ የካቲት ነው ፣ ቀኑ የሚካኤል ለት በአስራ ሁለት ፣ዓመቱ 1929 - ጣሊያኖች አዲስ አበባን በቁጥጥር ስር አድርገናል ብለው የተዝናኑበት ወቅት ነበር። ፋሽሽቶች ኢትዮጵያን በቁጥጥር ስር አውለናል በማለት በዓለም መንግሥታት ውስጥ ፕሮፖጋንዳቸውን በሚነፉበት ዘመን ነበር። እውነቱ ግን ከዚህ የተለየ ነበር። ለጣሊያኖች ድብቅ በሆነ ሁኔታ አፍንጫቸው ላይ መሪያቸውን ግራዚያኒን ለመግደል ሴራው ተጠንስሶ አልቋል። ለጣሊያኖች ታማኝ የሚመስሉ ግን ከአርበኞች ጋር ግንኙነት የነበራቸው ወጣቶች በዓለም ፊት ይህንን ቅጥፈት ለማጋለጥ ዝግጅቱን ጨርሰው ነበር።

ግራዚያኒ የጣሊያን መንግሥት አትዮጵያን እንዲመራ የሾመው የጣሊያን ንጉስን ልጅ መወለድን (Vittorio Emanuele, Prince of Naples ) ምክንያት በማድረግ ለእኔ ቢጤዎች እርዳታ እስጣለሁ በማለት በከተማው ውስጥ የሚገኙ ደሃዎችን ሰብስቦ ነበር። በዚህ ወቅት ቆራጦቹ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም፣ ስምዖን አደፍርስ ፣ ለጥይበሉ ገብሬ ወዘተ. . . ለመጨረሻው ፍልሚያ ተዘጋጅተዋል። ዝግጅቱ ሲጀመር የፈንጂ ድምጽ ይሰማል። ግራዚያኒ ቆስሎ ይወድቃል። ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ጭፍጨፋው ይጀመራል። ሁለቱ ጀግኖች በስምዖን አደፍርስ መኪና ተጭነው ወደ ደብረ ሊባኖስ ይሄዳሉ። ግራዚያኒ ይህንን ካወቀ በኋላ በፊትም ሊያጠፋው የሚፈልገውን ገዳም ለመደምሰስ ጥሩ ምክንያት አገኘ።በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር ደብረ ሊባኖስ ውስጥ ጭፍጨፋውን በሰፊው ያካሄዳል። በሜይ 18/1937 ሌሊት ደብረሊባኖስ ይከበብና ቀሳውስቱ ይታሰራሉ። 21/1937 በግራዚያኒ ወታደሮች ይረሸናሉ። በዚህ ቀን 2000 በላይ ካህናትንና የደብሩን ነዋሪዎችይጨፈጨፋሉ።



ይህንን ሁሉ ጭፍጨፋ የመራው ማነው? ሩዱልፎ ግራዚያኒ ይባላል። ግራዚያኒ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነሐሴ 11 / 1882 ተወልዶ በ ጥር 11/1955 ሮማ ውስጥ ሕይወቱ አልፋለች። ግራዚያኒ 1930 – 34 ሊቢያ

ውስጥ የጣሊያን ጦርን መርቷል። 1935 – 1936 የጣሊያን ሶማሌን ገዢ ሆኖ ተመድቧል። 1936 -37 የኢትዮጵያ ገዚ ተደርጎ በጣሊያኖች ተሹሞ ነበር። በዚህ ወቅት ግራዚያኒ ከላይ በተጠቀሰው የአርበኞች እንቅስቃሴ ምክንያት በሃገራችን የካቲት 12 ጭፍጨፋ ተብሎ በሚታወሰው በአዲስ አበባ ብቻ ከ30ሽህ ሕዝብ በላይ የተጨፈጨፋበትን እንቅስቃሴ የመራ ነው። ሩዶልፎ ግራዚያኒ ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረገውን ጭፍጨፋ በሚመለከት ምንም ፍርድ ያልተቀበለ ነው። ከነግፉ በነጻ ኖሮ የሞተ ነው። ምንም እንኳን በ1950 የ19 ዓመት ፍርድ ቢፈረድበትም በዛው ዓመት ተፈቷል።

በዚህ የሬዲዮ ፕሮግራም ገብረሥላሴ የሚጥረው የደብረሊባኖስ እልቂትን የተካሄደበትን ቀን ለማስታወስ ነው።

ካርሜሎ(ገብረሥላሴ) ከዛ በኋላ በብዙ ኢትዮጵያን በሚመለከቱ ስብሰባዎች ላይ እንድገኝ ረድቶኛል። ጥልቅ የሆነው የሃገራችን እውቀቱ ሃገሪቷን እንዲወዳት አድርጎታል። ጣሊያን ውስጥ እንደ ገብረሥላሴ ፣ እነደ ሦስቱ ወጣቶች ዓይነት እውነተኛ ዴሞክራቶችን ስናገኝ። በጎን ደግሞ እንደ አፊሌ ከተማ ከንቲባ ዓይነት የፋሽሽት ደጋፊዎች አሉበት። ስለዜጎቻን ሁኔታ ደግሞ በሚቀጥለው ክፍል እንመለከታለን። ታዕምራዊው የሮም ከተማን ከነታዕምሮቹ እንዳስሰዋለን።

ትግሉ በሁሉም መልኩ ይቀጥላል።

ስለ ሃገራችን የሚያስቡ ሁሉ በሰላም ይክረሙ።

ግንቦት /2014 ሮማ
ይቀጥላል
beljig.ali@gmail.com